# የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና
## የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ
## ቁጥር 477/2013

ጥቅምት 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ቁጥር477/2013**

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሙዚየም ማቋቋሚያ

## የሙያና የብቃት  ማረጋገጫ  አሰጣጥ መመሪያ

ሙዚየሞች የአንድን አገር ሕዝቦች ባህላዊና ታሪካዊ እንዲሁም ሃይማኖታዊ መገለጫ የሆኑ ቅርሶችን በማሰባሰብ እየጠበቁና እየተንከባከft ለጐብኚዎች፣ ለትምህርት፣  ለጥናትና ምርምር ሥራ እንዲሁም ለመዝናኛነት እንዲውሉ የሚያደርጉት አስተዋፅዖ  ከፍተኛ በመሆኑ፤

በሀገራችን የሚገኙና ወደፊትም የሚቋቋሙ ሙዚየሞች ቅርሶችን በቋሚነት  ከማቅረብም በላይ በተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ አዝናኝና ትምህርት ሰጭ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀት፣ የባህል መለዋወጫና የጋራ መግባቢያ መድረኮች በመሆን ወቅታዊ አገር አቀፍና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችንና እውነቶች በሚገባ እንዲያካሂዱ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ  በመገኘቱ፤

ሙዚየሞች ዘመናዊ አሠራሮችን ተከትለው በመልካም የውድድር መድረክ ውስጥ በመሆን ዓለም ከደረሰበት ዘመናዊ አሠራር ጋር እንዲራመዱ ማድረግ  አስፈላጊ   በመሆኑ፤

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣንና በሀገሪቱ በሚገኙ የሙዚየም  ባለይዞታዎች  መካከል ሊኖር የሚገባው ህጋዊና ተመጋጋቢ የሥራ ግንኙነት ግልፅ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ፣ ሙዚየሞችም ተወዳዳሪ ሆነው ለሀገሪቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እድገት የበኩላቸውን የሚያበረክቱበትን አቅም መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ   በመገኘቱ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 15 እና 46 ንዑስ    አንቀፅ 2 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል
## አንድ

# ጠቕላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ" ቁጥር 477/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በአዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀጽ 3 የተሰጠው ትርጓሜ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ሙዚየም"** ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ያልሆነ ቅርሶችን የሚሰበስብ፣ የሚጠብቅና የሚጠግን ለምርምርና ጥናት፣ ለማስተማሪያና ለመዝናኛነት ስብስቦችን በሚገባ አዘጋጅቶ ለኅዝብረተሰft አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡
2. **"የኢትኖግራፊ ሙዚየም"** ማለት የብሔሮች ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ወይም የአንድን ብሔር ባህላዊ እሴቶች የሚገልፁ ቅርሶች በማሰባሰብ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡
3. **"የስነጥበብ ሙዚየም"** ማለት የስዕል፣ ቅርፃ ቅርፅ ሌሎችንም የፈጠራ ሥራዎች ለማሳየት የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡
4. **"የታሪካዊ ዘመን ሙዚየም"** ማለት የታሪካዊ ቅርሶችን አሰባስቦ የሚያሳይ ሙዚየም ነው፡፡
5. **"የአርኪዎሎጂ ሙዚየም"** ማለት ከመሬት ውስጥ በሳይንሳዊ መንገድ በቁፋሮ የተገኙ ቅርሶችን አሰባስቦ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡
6. **"የፖስታ ሙዚየም"** ማለት የአንድ ሀገርን የየዘመኑን የፖስታና ቴምብር ህትመቶችን አሰባስቦ የሚያሳይ ሙዝየም ነው፡፡
7. **"ወታደራዊ ሙዚየም"** ማለት የአንድን ሀገር ወታደራዊ ሂደቶችንና ክንውኖችን ታሪክ በማሰባሰብ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡
8. **"ኦፕን ኤር ሙዚየም"** ማለት ታሪካዊ ክስተቶችን ወይም ባህላዊ ክንዋኔዎች ወይም ተፈጥሮአዊ ኩነቶች ወይም የሰው ዘር አመጣጥን የሚያሳይ የመካነ ቅርስ ስፍራ ነው፡፡
9. **"ልዩ ሙዚየም"** ማለት የተወሰነ ክስተትን ወይም ጭብጥን መሰረት ያደረገ

ሙዚየም ነው፡፡

10. **“የተፈጥሮ ቅርስ ሙዚየም”** ማለት የአንድን ሀገር ግብረ እፅዋትና እንስሳት ወይም የየዘመኑን የተፈጥሮ አካባቢን ለውጦችና መስተጋብሮች ታሪክ በማሰባሰብ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡

11. **“የሰው ዘር ምንጭ ሙዚየም”** ማለት የሰው ዘር አመጣጥ ታሪክን ከጥንተ ዓለም/ፓሊዮንቶሎጂ ወይም ፓሊዮአንትሮፖሎጂ/ ጀምሮ ያሉ ቅሪተ አካላትን፣ መገልገያ መሳሪያዎችን አሰባስቦ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡

12. **“የአጠቃላይ ስብስብ ሙዚየም”** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የስብስብ አይነቶችን ማለትም የኢትኖግራፊ፣ የስነ ጥበብ፣ የታሪክ ዘመን፣ የአርኪዎሎጂ ስብስቦች ያሉት ሆኖ እነዚህን ለእይታ የሚያቀርብ ነው፡፡

13. **“ሃይማኖት ተቋማት ሙዚየም”** ማለት፣ በሃይማኖት ተቋማት ባለይዞታነት ተመስርቶ የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡

14. **“የመታሰቢያ ሙዚየም”** ማለት አንድን ክስተት ወይም ታሪክ ወይም፣ የግለሰብ/የግለሰቦችን ታሪክ ወይም ሂደት ለማስታወስ የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡

15. **“የግል ሙዚየም”** ማለት በግለሰብ ባለይዞታነት የሚተዳደር ሙዚየም ነው፡፡

16. **“የትርኢት ገላጭ ባለሙያ”** ማለት በሙዚየም ውስጥ የተዘጋጀ ቋሚም ሆነ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽንን ለጎብኚዎች በመግለጽ ወይም በማስረዳት ሙያ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ነው፡፡

17. **“የትርኢት ዝግጅት ባለሙያ”** ማለት በሙዚየም ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ኤግዚቢሽኖችን የሚያዘጋጅ ባለሙያ ነው፡

18. **“የሙያና ብቃት ማረጋገጫ”** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የሙዚየም አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው

19. **“የሙዚየም ባለይዞታ”** ማለት ህጋዊና ሙያዊ በሆነ መንገድ ሙዚየም አቋቁሞ የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡

20. **“የሙዚየም ደረጃ”** ማለት ሙዚየሞች ባላቸው ስብስብ ዓይነት በአደረጃጀታቸው፣ በሰው ኃይል ስብጥራቸው የሚሰጣቸው ደረጃ ነው፡፡

21. **“የሙዚየም አይነት”** ማለት ሙዚየሞች በስብስባቸውና በሚሰጡት አገልግሎት ወይም በባለይዞታነት ወይም በተደራጀበት ቦታ የሚለዩበት ወይም

የሚታወቁበት  መንገድ  ነው፡፡

22. **"ቅድመ እውቅና"** ማለት ከተቀመጡት መስፈርቶች በከፊል መሟላታቸው ሲረጋገጥ የሚሰጥ የእውቅና ዓይነት ነው፡፡
23. **"እውቅና"** ማለት በየደረጃው የተቀመጡት መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ መሟላታቸው ሲረጋገጥ የሚሰጥ እውቅና ነው፡፡
24. **"በሙዚየም መልክ የተደራጀ ተቋም"** ማለት ቅርሶችን ወይም ልዩ ልዩ መስተጋብሮችን በቋሚነት ለማሳየት የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡
25. **"ሚኒስቴር "** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡
26. **"ባለስልጣን"** ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
27. **"አዋጅ"** ማለት የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ ዓዋጅ ቁጥር 209/1992 ነው፡፡
28. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
29. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በተቋቋሙ እና በሚቋቋሙ ሙዝየሞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>የሙዚየም አደረጃጀት</u>

## 4. <u>ሙዚየም ስለማቋቋም</u>

1. ሙዚየም በግል ወይም በማህበር ወይም በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም በሃይማኖት ተቋማት ሊቋቋም ይችላል፡፡
2. የሰው ዘር አመጣጥን የሚያሳይ ሙዚየም ወይም የፖሊዮንቶሎጂና የፖሊዮአንትሮፖሎጂ አርኪዎሎጂ ሙዚየሞች በመንግሥት አካላት ብቻ ይቋቋማሉ፡፡
3. ሙዚየም ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡
4. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተቋቋሙ ሙዚየሞች ፀንተው ይቆያሉ፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀው ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከተውን መመዘኛ የማሟላት ግዴታ አለባቸው፡፡

## 5. የሙዚየም ዓይነቶችና ደረጃዎች

1. የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የሙዚየም

   አይነቶች፡- ሀ. የኢትኖግራፊ ሙዚየም

   ለ. የሥነ ጥበብ ሙዚየም

   ሐ. የታሪክ ዘመን

   ሙዚየም መ.

   የአርኪዎሎጂ ሙዚየም ሠ.

   አጠቃላይ ሙዚየም

   ረ. ወታደራዊ ሙዚየም

   ሰ. የፖስታ ሙዚየም

   ሸ. የሃይማኖታዊ ተቋማት ሙዚየም

   ቀ. የመታሰቢያ ሙዚየም

   በ. የሰው ዘር ምንጭ ሙዚየም

   ተ. የተፈጥሮ ቅርስ ሙዚየም

   ቸ. ልዩ ሙዚየሞች

   ኀ. ኦፕን ኤር ሙዚየም እና

   ነ. በሙዚየም መልክ የተደራጀ ተቋም

2. የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የሙዚየም ደረጃዎች

   ሀ. ደረጃ 1 ሙዚየም

   ለ. ደረጃ 2 ሙዚየም

   ሐ. ደረጃ 3

   ሙዚየም

3. የሙያና የብቃት ማረጋገጫ እንደ ሙዚየሞቹ የእድገት ደረጃ በመጀመሪያ በዚህ መመሪያ ውስጥ ለተጠየቀው የሙዚየም ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት ሰባ አምስት በመቶ ሲያሟላ የቅድመ ዕውቅና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት በመቀጠልም ለአንድ ዓመት በሚሰጠው የቆይታ ጊዜና ግምገማ

**መሠረት የሙሉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ ይሆናል፡፡**

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን የሙዚየም አይነቶች መሠረት በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
5. ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ ሙዚየም ለሚያቋቁሙ አካላት ክልሎች ፍቃድ መስጠት ይችላሉ፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ቁጥር 2 ላይ የተመለከቱት የሙዝየም ደረጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ከደረጃ 3 ቀጥሎ በልዩ ሁኔታ የሚታይ በሙዚየም መልክ የተደራጁ የቅርስ ስብስብ ማእከላት የቅርብ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ወደ ደረጃ ሶስት የሚገ[illegible]በት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ሙዚየም ማቋቋሚያ መስፈርቶች

### 6. ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ የወል መስፈርቶች

ማንኛውንም አይነት ሙዚየም ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. **ደረጃ 1 ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

   ሀ. ቅርሶቹ የሚታዩበት ሥፍራ በማሳያ ግብዓቶች በሾው ኬዝ፣ ፓናል፣ መብራቶችና ለአውደ ርዕይ አገልግሎት በሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟላ መሆን አለበት፡፡

   ለ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ ከ300 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬት ላይ ያረፈ መሆን ይኖርበታል፡፡

   ሐ. ሙዚየሙ ለጐብኚዎች አመቺ የሆነ፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት ቅርበት ያለው፣ ቅጥር ግቢው ለመኪና ማቆሚያ በቂ ስፍራ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

   መ. ሙዚየሙ የሰለጠነ የቅርስ እንክብካቤና ጥገና፣ የቅርስ አሰባሳቢ፣ ቢያንስ አራት የትርኢት ገላጭ፣ ሁለት የጥበቃ ባለሙያዎችና የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችን ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

   ሠ. የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ አስተማማኝ የጥበቃ [illegible]ድን፣ የእሳት መከላከያ፣ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ አላርም፣ የመውጫ በርና ዘመናዊ የእሳት ማጥፊያ ያለው፣

ረ. የቅርስ ክምችት ክፍል፣ ላቦራቶሪ ክፍል፣ የኬሚካልና የቅርስ ጥገና ክፍል ያለው፣

ሰ. ከሀያ ያላነሱ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት እነዚህም የመረጃ ዴስክ፣ የትኬት መቁረጫ፣ የእንግዳ ማረፊያ፣ የቋሚና ጊዜያዊ ኤግዚቢሽን አዳራሽ፣ የኦዲዮቪዥዋል፣ የደህንነት ጥበቃ ክፍል፣ ቤተመፃሕፍት ክፍል ያለው፣

ሸ. ሙዚየሙ ስለ አጠቃላይ አገልግሎቱ ማለትም የመግቢያ ዋጋ ለአዋቂ፣ ለተማሪ፣ ለውጭ ዜጎች፣ በሰሌዳ ያሳወቀ እንዲሁም ስለ እያንዳንዱ ትርኢት ክፍል በቂ መግለጫና አቅጣጫ ጠቋሚ ያዘጋጀ፣

ቀ. ወለሉ ከድምፅ፣ ከንዝረት፣ ከመንሸራተት የሚከላከልና ቀለሙ ለእይታ የማይረብሽ የሆነ፣

በ. ሙዚየሙ በዳይሬክተር ወይም ሥራ አስኪያጅ የሚመራ፣

ተ. በፆታ የተከፋፈለ የመፀዳጃ ቤት ያለው፣

ቸ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች ያለው፣

ኀ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ ያለው፡፡

ነ. በቂ የአየር ማስገቢያ ያለው፣

ኘ. ሠራተኞችና ጉብኚዎች የሚስተናገዱበት ካፍቴሪያ ያለው

እና አ. ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የሆነ፣

2. **ደረጃ 2 ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

ሀ. ቅርሶቹ የሚታዩበት ስፍራ በማሣያ ግብዓቶች ማለትም በሾው ኬዝ፣ ፓናል፣ መብራቶችና ለዓውደ ርዕይ አገልግሎት በሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ ከ200 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬት ላይ ያረፈ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. ሙዚየሙ ለጐብኚዎት አመቺ በሆነ ሥፍራ የሚገኝ ሆኖ ለትራንስፖርት አገልግሎት ቅርበት ያለውና ቅጥር ግቢው በቂ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ያለው፣

መ. ሙዚየሙ የሰለጠኑ የሙዚየም አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች፣ የትርኢት ገላጭ፣ የቅርስ አሰባሳቢ ባለሙያዎች ያለው የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ አስተማማኝ የጥበቃ ባለሙያዎችና የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችን ያሟላ፣

ሠ. ከ15 ያላነሱ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት እነዚህም የመረጃ ዴስክ፣ የትኬት መቁረጫ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ የደህንነት ጥበቃና ሌሎች የአስተዳደር አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት፣

ረ. የቅርስ ክምችት ክፍል ያለው፤

ሸ. ሙዚየሙ ከቅርስ አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ባለው ሙያ በሰለጠነ ዳይሬክተር/ሥራ አስኪያጅ የሚመራ፣

ቀ. የሙዚየሙ ወለል ከንዝረት፣ከድምፅ፣ከማንሸራተት ነፃ የሆነና ለእይታ የማይረብሽ፣

በ. በፆታ የተከፋፈለ መፀዳጃ ቤት ያለው፡፡

ተ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች ያለው፣ ቸ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ ያለው፡፡

ኀ. በቂ የአየር ማስገቢያ ያለው፣

ነ. ሠራተኞችና ጉብኚዎች የሚስተናገዱበት ካፍቴሪያ ያለው ኘ. ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የሆነ፣

## 3. <u>**ደረጃ 3 ሙዚየም ለማቋቋም**</u>

ሀ. ሙዚየሙ ለአውደ ርዕይ በሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማለትም በሾው ኬዝ፣ ፓናል፣ ፔዴስታሎች የተሟላ ሊሆን ይገባል፡፡

ለ. ለሙዚየሙ የሚሆን ህንፃ ከ100 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬት ላይ ያረፈ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. ሙዚየሙ ለደህንነት አስተማማኝና ለትራንስፖርት አመቺ በሆነ መንገድ ሥፍራ መገኘት አለበት፡፡

መ. ከስምንት ያላነሱ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያለው ማለትም የትኬት መቁረጫ የእንግዳ መቀበያ፣ የጥበቃ ክፍል፣

**የአስተዳደር አገልግሎት መስጫ፣ የቅርስ ክምችት ክፍል ያለው፣**

ሠ. የትርኢት ገላጭ ባለሙያ ያለው፣

ረ. በያታ የተከፋፈለ መፀዳጃ ቤት ያለው፣

ሸ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች

ያለው፣ ቀ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ

ያለው፡፡

በ. በቂ የአየር ማስገቢያ ያለው፣

ተ. ሠራተኞችና ጉብኚዎች የሚስተናገዱበት ካፍቴሪያ ያለው

ቸ. ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የሆነ

## 7. <u>የኢትኖግራፊ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

1. **ደረጃ 1 የኢትኖግራፊ ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "አ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትም መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ አሠራር የአገሪቱን ወይም የአካባቢውን ባህል የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ5000 ያላነሰና ብዛቱና ዓይነቱ የአገሪቱን ወይም የሚያቋቁመውን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡

ሐ. ስብስft የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የሃይማኖት እኩልነት የሚያከብርና የተሟላ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

2. **ደረጃ 2 የኢትኖግራፊ ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል “ሀ” እስከ "ኘ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ አሠራሩ የአገሪቱን ባህል የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ3000 ያላነሰና ብዛቱና አይነቱ የአገሪቱን ወይም የሚቋቋምበትን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

ሐ. የቅርሶችን ስብስብ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሃይማኖትን እኩልነት የሚያከብርና የተሟላ መረጃ ሊኖረውይገባል፡፡

3. **ደረጃ 3 የኢትኖግራፊ ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል “ሀ” እስከ "ቸ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ አሠራር የአገሪቱን ወይም የአካባቢውን ባህል የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ 1000 ያላነሰና ብዛቱና ዓይነቱ የአገሪቱን ወይም የሚቋቋምበትን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

ሐ. የቅርሶቹ ስብስብ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኃይማኖትን እኩልነት የሚያከብርና የተሟላ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

## 8. <u>የስነ ጥበብ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

1. **ደረጃ 1 የስነ ጥበብ ሙዝየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "አ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ከ250 ያላነሱ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነ ጥበብ ቅርሶች ስብስብ ያለው፣ ለ. በስነጥበብ ሙያ የሰለጠኑ 3 ባለሙያዎች ያሉት፣

ሐ. የቅርፃ ቅርፅ ወይም ሃውልቶች ማስቀመጫ ፔድስታሎች ያሉት፡፡

2. **ደረጃ 2 የስነ ጥበብ ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል “ሀ” እስከ "ኘ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ከ175 ያላነሱ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነ ጥበብ ቅርሶች ስብስብ ያለው፣

ለ. በስነጥበብ የሰለጠነ ቢያንስ 2 ባለሙያ ያለው ፣

**ሐ. የቅርፃ ቅርፅ ወይም ሃውልቶች ማስቀመጫ ፔድስታሎች ያሉት፡፡**

3. **ደረጃ 3 የስነጥበብ ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል "ሀ" እስከ "ቸ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ከ100 ያላነሱ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነጥበብ ቅርሶች ስብስብ ያለው፣

ለ. በስነጥበብ የሰለጠነ ቢያንስ 1 ባለሙያ ያለው፣

ሐ. ለቅርፃ ቅርፅ ሥራዎች የራሱ የሆነ ማስቀመጫ ያለው፡፡

## 9. <u>የታሪክ ዘመን ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

1. **ደረጃ 1 የታሪክ ዘመን ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "አ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው ቅርሶች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ትክክለኛ ታሪክ በማስረጃ የያዘ፣

ለ. ቅርሶቹ የተለያየ ዘመን ታሪክ የሚያሳዩ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ ሚሰጡ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ሐ. ለአልባሳት ቅርሶች፣ ለጥንታዊ መጽሐፍት የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሳቁስ ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. ከ3 በላይ የሰለጠኑ የታሪክ ዘመን ባለሙያዎች

ያሉት፡፡ 2. **ደረጃ 2 የታሪክ ዘመን ሙዚየም ለማቋቋም፡-**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል “ሀ” እስከ "ኘ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው ቅርሶች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ትክክለኛ ታሪክ ከነማስረጃው፣

ለ. ቅርሶቹ የተለያየ ዘመን ታሪክን የሚያሳዩ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ የሚሰጡ፣

ሐ. ለአልባሳት ቅርሶች፣ ለጥንታዊ መጽሐፍት የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሰቁሶች ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. ከሁለት የማያንሱ የታሪክ ዘመን ባለሙያዎች ያሉት፡፡

3. **ደረጃ 3 የታሪክ ዘመን ሙዚየም ለማቋቋም**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል “ሀ” እስከ "ቸ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በየሚከተሉትን መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው ቅርሶች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ትክክለኛ ታሪክ ከነማስረጃው፣

ለ. ለታሪካዊ ስብስቦች አመቺ የሆነ የዐውደ ርዕይ ማሳያ ቁሳቁሶች ያለው ፣

ሐ. በቅርስ ወይም በታሪክ ዘመን የሰለጠነ ቢያንስ አንድ ባለሙያ ያለው፡፡

## 10. <u>የአርኪዎሎጂ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

1. **ደረጃ 1 የአርኪዎሎጂ ሙዚየም**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "አ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው የአርኪዎሎጂ ቅርሶች ትክክለኛ ታሪክ ማስረጃ የያዘ፣(በቁፋሮ የተገኙት ቅርሶችም ጥናትና ምርምር ተካሂዶባቸው ትክክለ ኛነታቸው የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል)

ለ. ቅርሶቹ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ የሚሰጡ፣ ሐ. ለቅርሶች የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሳቁስ ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. ከ3 በላይ የሰለጠኑ የአርኪዎሎጂ ባለሙያዎች ያሉት፡፡

2. **ደረጃ 2 የአርኪዎሎጂ ሙዚየም**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል “ሀ” እስከ "ኘ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው የአርኪዎሎጂ ቅርሶችን ትክክለኛ ታሪክ ማስረጃ የያዘ፣(በቁፋሮ የተገኙት ቅርሶችም ጥናትና ምርምር ተካሂዶባቸው ትክ

ክለኛነታቸው የተረጋገጠ  መሆን ይኖርበታል)

ለ. ቅርሶቹ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ የሚሰጡ

ሐ. ለቅርሶች የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሳቁስ ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. ከሁለት የማያንሱ የሰለጠኑ የአርኪዎሎጂ ባለሙያዎች ያሉት፡፡

3. **ደረጃ 3 የአርኪዎሎጂ ሙዚየም**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል “ሀ” እስከ "ቸ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው የአርኪዎሎጂ ቅርሶች ትክክለኛ ታሪክ ማስረጃ የያዘ፣(በቁፋሮ የተገኙ ቅርሶችም ጥናትና ምርምር ተካሂዶባቸው ትክክ ለኛነታቸው የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል)

ለ. ቅርሶቹ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ የሚሰጡ፣

ሐ. ለቅርሶች የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሳቁስ ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. በአርኪዎሎጂ መስክ የሰለጠነ ቢያንስ አንድ ባለሙያ ያለው፡፡

## 11. <u>አጠቃላይ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1. **ደረጃ 1 አጠቃላይ ሙዚየም**

ከላይ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "አ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ አራት የስብስብ ዓይነቶችን መያዝ ይኖርበታል፣ ለ. ለእይታ የሚቀርቡት ቅርሶች እንደ አይነታቸው የየራሳቸው ክፍሎች ለየብቻ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፣

ሐ. የሙዚየሙ የትርኢት ክፍሎች የራሳቸው የክፍል መግለጫ የተዘጋጀላቸው መሆን አለበት፣

መ. በሙዚየም፣በታሪክ፣በአንትሮፖሎጂ፣በስነጥበብና በዲዛይን አርኪዎሎጂ ወይም በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠኑ ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ያለው መሆን አለበት፡፡

2. **ደረጃ 2 አጠቃላይ ሙዚየም**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል “ሀ” እስከ "ኘ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ 3 ዓይነት የስብስብ ዓይነቶችን መያዝ ይኖርበታል፣

ለ. ለእይታ የሚቀርቡት ቅርሶች እንደ አይነታቸው የየራሳቸው ክፍሎች ለብቻ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፣

ሐ. የሙዚየም የትርኢት ክፍሎች የየራሳቸው የክፍል መግለጫ የተዘጋጀላቸው መሆን አለበት፣

መ. ሙዚየሙ የሰለጠኑ ቢያንስ 2 የታሪክ፣ የአንትሮፖሎጂና የሥነ ጥበብና የትርኢት አዘጋጅ ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል፡፡

3. **ደረጃ 3 አጠቃላይ ሙዚየም**

በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል "ሀ" እስከ "ቸ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ 2 ዓይነት የስብስብ አይነቶች ማደራጀት አለበት፣

ለ. ለእይታ የሚቀርቡ ቅርሶች፣ የየራሳቸው ክፍሎችና መግለጫ የተዘጋጀላቸው፣

ሐ. ሙዚየሙ ቢያንስ በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ በታሪክ፣ ወይም አንትሮፖሎጂ፣ ወይም ሥነጥበብና ዲዛይን ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ ቢያንስ 1 የትርኢት ባለሙያዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

## 12. ስለ ሌሎች የሙዚየም ዓይነቶች

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1/ከረ-ነ/ የተዘረዘሩት የሙዚየም ዓይነቶች በአንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች እና እንደ ሙዚየም አይነቱ አስፈላጊ የሆኑትን የቅርስ ስብስቦች ሲያሟሉ የደረጃውን የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ያገኛሉ፡፡
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሙዚየሞች በሚያቀርቡት መረጃ መሠረት ደረጃቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

# ክፍል አራት

# መብትና

# ግዴታዎች

## 13. የሙዚየም ባለይዞታ መብት

ማንኛውም የሙዚየም ባለይዞታ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. ቅርሶችን በውርስ ወይም በውሰት ወይም በግዥ ወይም በጥናትና ምርምር ወይም በአደራ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ   የማሰባሰብ፣
2. ከሚዘጋጀው ኤግዚቢሽን ወይም የሙዚየም አገልግሎት ወይም ከጥናትና ምርምር አገልግሎት ክፍያ የማግኘት፣
3. ሙዚየሙን የማሻሻል ወይም ተጨማሪ ቅርሶችን  የመሰብሰብ  ወይም ከሙዚየም አገልግሎት ጋር ተያያዥ  በሆነ  መልኩ  ጥናትና  ምርምር የማድረግ ሲምፖዚየም፣ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽን የማዘጋጀት፣
4. ለሙዚየሙ እድገት የማቀድ፣ በዚሁ መሠረት የመንቀሳቀስ፣ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችን የመክፈት፣ ከሚመለከተው መሥሪያ ቤት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት፣
5. የሙዚየሙን ደረጃ የማሻሻል፣ ከአንድ በላይ ሙዚየም  የማቋቋም፣

## 14. <u>የሙዚየም  ባለይዞታ ግዴታ</u>

ማንኛውም የሙዚየም  ባለይዞታ የሚከተሉት  ግዴታዎች  አሉበት፡፡

1. ቅርስን አስመልክቶ የወጡ ህጎችንና ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች የማክበር፣
2. ሙዚየሙ ሲዘጋ ወይም አገልግሎት መስጠቱን ሲያቋርጥ ወይም ቅርሱን ለተመሳሳይ ድርጅት ሲያስተላልፍ ወይም በማናቸውም  ሁኔታ  ሲዘጋ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በፅሑፍ የማሳወቅ፣
3. ቅርሶችን ለኤግዚቢሽን ሲያንቀሳቅስ ኢንሹራንስ  የመግባት፣
4. የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለሚያደርጉት ቁጥጥር የመተባበር፣
5. በሙዚየሙ ውስጥ ያሉ ቅርሶችን በሙሉ መረጃ የያዘ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የማደራጀት፣
6. በሙዚየሙ ውስጥ ያለውን የቅርስ ዝርዝር በየዓመቱ  ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፣
7. የተሰጠውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት  ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ  አለመስጠት፣
8. አገልግሎቱ የተቋረጠ ሙዚየም የምስክር ወረቀቱን ለባለስልጣኑ የመመለስ፣

9. በይዞታው ሥር ያሉት ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ፣

10. የሙዚየሙን የብቃት ማረገገጫ የምሥክር ወረቀት በየሁለት ዓመቱ የማደስ፣

11. ቅርሶቹ ለሀገራዊ ጉዳዩችሲፈለጉ የመተባበር፣

12. የቅርስ ስብስብ ፖሊሲ የማዘጋጀት፣

13. የሙዚየሙን ቅርሶች ያለ ሚኒስቴሩ ፍቃድ በማንኛውም ሁኔታ ከሀገር ያለማስወጣት፡

## ክፍል
## አምስት

## የምስክር ወረቀት ስለመስጠት፣ ስለማደስና

**መሰረዝ 15. የሙያና ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

1. ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ብቻ ሆኖ የሚከተሉትን ማስረጃዎች አመልካቹ ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

   ሀ. ሙዚየሙን ለማቋቋም የጠየቀው አካል ሙሉ ስም፣
   ለ. ሙዚየም የሚቋቋምበት ወይም የተቋቋመበት ቦታ ሙሉ አድራሻ፣
   ሐ. ሙዚየሙ የያዛቸው ወይም የሚይዛቸው የቅርሶች ዓይነትና መጠን፣ መ. የቅርሶቹ ዝርዝርና ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ፣
   ሠ. ለሙዚየምነት የተመረጠው ወይም የሚያገለግለው የህንፃ ዓይነት ስፋትና የክፍሎች ብዛት ወይም ኘላን፣
   ረ. የሙዚየሙ ተደራሽነት፣
   ሰ. የሙዚየሙ መቋቋም ለህብረተሰfftና ለሀገሪቱ ያለው ፋይዳ፣
   ሸ. ሙዚየሙ ያለው የሰው ኃይል ብዛትና የስልጠና ዓይነት፣
   ቀ. ሙዚየሙ ያሉት የማሳያ ግብዓቶችና የሀብት መጠን እና ሥራ ማስኬጃ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል “ሀ” እስከ “ቀ” የተጠቀሱትንና አስፈላጊ የተባሉ መረጃዎችን ሶፍት ኮፒና(በሲዲ) በሀርድ ኮፒ ከማመልከቻው ጋር ለባለስልጣኑ በአካል በመቅረብ፣ በፖስታ አድራሻ፤ በኢሜል ወይም በድህረገፅ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

3. የሙዚየም ማቋቋሚያ ብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው ማመልከቻው ለሚመለከተው ክፍል ከተመራለት በኋላ ለዚህ የተዘጋጀውን ቅጽ

ይሞላል፡፡ ይህም ቅጽ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከፊደል ሀ እስከ ቀ የተጠቀሱትን ያካትታል፡፡

4. የተሞላውን ቅጽ በመፈረምና ከቀረበው ማስረጃ ጋር በማያያዝ ይመልሳል፡፡?

5. ማንኛውም የሙዚየም ባለይዞታ የባለስልጣኑን የሙያና ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት አስፈላጊውን የማመልከቻና የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰነው መሠረት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 16. የሙያና ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ግምገማና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1. ለግምገማ የቀረበው ማመልከቻና ማስረጃዎች እንዲሁም የባለሙያዎች የመስክ አስተያየት በተሟላ ሁኔታ መስፈርቶቹን የሚያሟላ መሆኑ በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምስክር ወረቀቱ ይሰጣል፡፡
2. ለግምገማ የቀረበ ማመልከቻና ማስረጃ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው አካል መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በባለሥልጣኑ ይገለጽለታል፡፡ ደብዳቤው በተፃፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ ወይም አሟልቶ ካልቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡
3. በየጊዜው የሙዚየምን ደረጃና ዓይነት ለማሻሻል የሚፈልጉ የሙዚየም ባለይዞታዎች በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት የሚስተናገዱና የምስክር ወረቀት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

## 17. ክትትልና ቁጥጥር

1. ሙዚየም ለሚያቋቁሙና ላቋቋሙ አካላት በባለስልጣኑ ባለሙያዎች አማካኝነት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሙያዊ ድጋፍ ክትትልና ግምገማ ያካሂዳል፡፡
2. ሙዚየም ለማቋቋምና የኤግዚቢሽን ዝግጅትን አስመልክቶ ከባለስልጣኑ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ የሚጠይቅ አካል የቀጣዩ ዓመት በጀት ከመያft ከአንድ ወር በፊት በማመልከቻ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. የባለስልጣኑን ባለሙያዎች እገዛ በአስቸኳይ የሚፈልግ ከሆነ ጠያቂው አካል ሙሉ ወጭውን በመሸፈን የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችን በማስፈቀድ ሊጠቀም ይችላል፡፡
4. የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የሙዚየሞችን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ ወይም ለጥናት ወይም የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎትን በተመለከተ በተለያየ ጊዜ

ወደ  ሙዚየም  በመሄድ ክትትልና  ቁጥጥር  ያደርጋሉ፡፡

5. በክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት ወቅት የማሳያ ሁኔታ፣ የማሳያ ግብዓቶች ለጐብኝዎች የሚሰጥ አገልግሎት፣ መብራቶች፣ የቅርሶች ደህንነት የባለሙያዎች ብቃትና አጠቃላይ ሂደቶች ተገምግመው የሚሻሻሉበት ሁኔታ ሀሳብ ይቀርባል፡፡

## 18. <u>የምሥክር ወረቀት ስለማደስ</u>

የሙዚየም የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ከባለስልጣኑ ያገኘ ሰው ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማደስ አለበት፡፡ ክፍያውም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ይፈፀማል፡፡

## 19. <u>የምሥክር ወረቀት ስለመሠረዝ</u>

1. የምስክር ወረቀት ሊያሠርft የሚችሉ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው
   ሀ. ሙዚየሙን ያቋቋመው ሰው በራሱ ፍቃድ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስ
   ለ. ሙዚየሙ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ እየሠራ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
   ሐ. የሙዚየሙ ቅርሶች ለአደጋ የተጋለጡ እንደሆነ፣ ሙዚየሙ ከፋይናንስ እጥረት፣ ከባለሙያ አለመኖር፣ ከደህንነት አኳያ ሊሠራ የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ፣
   መ. የምስክር ወረቀት የተሰጠው አካል በአግባft እየሠራበት አለመሆኑን በተግባር ሲረጋገጥ፡፡
2. የሙዚየም ማቋቋሚያ የምስክር ወረቀት ከመሠረft በፊት ላቋቋመው አካል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና የ3 ወር የማስተካከያ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሁኔታዎች የማይስተካከሉ ከሆነ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡ ቅርሶቹም ህጋዊ በሆነ መንገድ ወደ መንግሥት ይዞታነት ይዛወራሉ፡፡
4. ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ በይዞታው ሥር የሚገኙ ቅርሶችን ለሦስተኛ ወገን መተላለፉ በማስረጃ ከተረጋገጠ ያለ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የምስክር ወረቀቱ ይሠረዛል፡፡

## 20. ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ

በደረጃ አመዳደብ ወይም በምስክር ወረቀት መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 22. ቅጣት

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

## 23. የስራ ማንዋል ስለማውጣት

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ዝርዝር የሆነ የስራ ማንዋል ያወጣል፡፡

## 24. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ_______________ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡